EthioLion

# « ወንድ ልጅ በልቡ እንጂ በዐይኑ አያለቅስም »

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

« ኧረ ጎበዝ ! እህም ነው !

ጎበዝዬ ! እህም ነው !

የጎበዝ ወዳጅ ታስታውቃለች፤

አፋፍ ላይ ቆማ በለው ትላለች፤

የፈሪ ወዳጅ ታስታውቃለች፤

ከማጀት ሆና ቂጧን ታካለች........ » ወዘተ ::

እንደ ዛሬው አገራችን የወንድ ድርቅ ሳይመታት፤ ዱሮ ያኔ ጥንት ባገራችን በኢትዮጵያ ጀግኖች ላገራቸው ድንበር፤ ለነፃነታቸው መከበር ወኔያቸው ተቆጥቶ የወራሪን ቅስም ለመስበር፤ ያገር ድንበር ለማስከበር፤ ሲነሱ ከሚያሰሙት የሽለላና የቀረርቶ እንዲሁም ፉከራዎች መሃከል ትዝ ያለኝን ነው ቀንጨብ ያረኩት ::

ታዲያ ዛሬ፤ ዛሬ፤ አለመታደል ሆነና፤ አገራችን ኢትዮጵያ ወኔው የሚሰነፍጠው ጀግና ቀርቶ፤ ከማጀት ሆኖ የሚያለቅስ ወንድ መናኸሪያ ሆናለች ::

ለዚህ ይሆን « ወንዱን ወንድ አማረው » የሚል ሃረግ እየተነገረ ያለው ?

እንግዲያው ለጀግኖች እህቶቻችን ቦታውን እንልቀቅና: በነሱ መሪነት ታግለን አገራችንና ሕዝባችንን ነፃ እናውጣ :: እነሱ በመጀምውሪያ እናት፤ ቀጥሎም እህት፤ ከዚያም ሚስትና ሴት ልጅ በመሆን : ከጎናችን ሳይለዩ መከራውን ተቋድሰዋል ታዲያ በወንዱ ካልተሳካ በሴት እህቶቻችን ወይም ልጆቻችን ነፃ ብንወጣ ምንድነው ሃጢያቱ? እንዲያውም ትልቁ ሃጥያት በገዛ አገር ሁለተኛ ዜጋና የበይ ተመልካች መሆኑ ነው ::

ደግሞስ፤ ቆሞ የሸና ሁሉ ወንድ አለመሆኑን እያየነው ነው: ታዲያ ቁጭ ብሎ የሸና ሁሉ ሴት አለመሆኑን ቢያሳዩን ምንድነው ችግሩ?!

« ሞት መጣ ! » ቢሉት « ግባ በለው ! » የሚለው ያ ትውልድ አልፎ፤
ሞት መጣ ሲሉት፤ ከማጀት የሚወተፍ ትውልድ ተፈጠረ፤ ከሞት ያመልጥ ይመስል !

የወንድነት መረቁ ከውስቱ የተንጠፈጠፈ ትውልድ፤ ወኔው በመዛጉ ሲጢጥ፤ ሲጢጥ እያለ ስለሚያስቸግረው ለአገሩ ዘብ መቆም አይሆንለትም፤ ጫት ሲያለፋጭቅ እየዋለ ማታ ልጓም በሌለው በአረቄ ፈረስ የቅንዝር በትሩን ገትሮ እየጋለበና እየተጋለበ በድኑን ይንዘባረራል ::

EthioLion

*የማይቻለውን ሁሉ መቻል የለመደ ትውልድ ሰብዕናውን አዋርዶ ወደ አህያነት ዝቅ ስላለ ያሻቸውን ሁሉ ቢጭኑት ገጣባውን አይቆጠቁጠውም፤ እናም ዝም ብሎ መደብለሉን ይቀጥላል ። ይህ በልመና ሰንዴ የተረገዘ ትውልድ የሚወለደው ከነጥርሱ ስለሆነ ወዲያው እንደተወለደ ማጓመጥ ስለሚጀምር ከአይምሮው ይልቅ ሆዱ ይሰፋል፤ እናም ነፃነትንም በልመና እንዲሰጡት ያንጋጥጣል እንጂ በትግሉ ውጤት ለማግኘት አይደፍርም ።*

*ከልባቸው ፍቅር የማይፈልቅ፤ ፍትሕ በአይምሯቸው የማይጠነሰስ፤ በአንደበታቸው ሃቅ የማይነገር፤ እጃቸው ቃታ ለመሳብ የፈተነ፤ ሆዳቸው እንደመቃብር ያገነውን ሁሉ የሚውጥ፤ እግሮቻቸው እሬሳ ተራምዶ ለመሄድ የፈጠኑ፤ ባጥንታቸው የቀሩ እናቶችና ሕፃናት ለቅሶ ልባቸውን የማይሸረሽረው፤ ከራሳቸው በቀር ሁሉን እንደ ጠላት የሚቆጥሩ፤ ማሰብን የገደቡ፤ መናገርን የሚፈሩ፤ መጻፍን የኮነኑ፤ አንድነትን ጠልተው በጎሳና በሃይማኖት የሚከፋፍሉ፤ ላገር ሳይሆን ባገርና በሕዝብ ላይ የመጡ እኩይ ፍጡሮችን እምቢ ማለት ያባት፤ የአያትና የቅም አያት መሆኑ ቀርቶ፤ ሁሉን መከራ ተሸካሚ፤ ሁሉን በደል ተቀባይ፤ ሁሉን እሺ ባይ፤ ትውልድ ሲገኝ ያዲያ ምነው አይጋለብ፤ ምነው አይደበለል ጃል ?!*

*የጥንት ወጉ፤ ደሞ ገለሌ ! ዘራፍ ! አሻፈረኝ ! እቢኝ ! ሸለላው፤ ቀረርቶውና ፉከራው ቀርቶ፤ ዛሬ ፡ ዛሬ ፡ እንዳው ይሁና !! ችሎ ማደር፤ ዛሬን ሳይኖሩ ሌላም ቀን አለና፤ የበደለን አትንካ፤ የሰው ቢጎድል አምላክ ይዳኛል፤ የባሰም አለና፤ ከዚህ የባሰ ምን እስኪመጣ እንደሚጠበቅ ባላውቅም፤ እንዲህ እንዲህ እየተባለ ወኔ ሰላቢና ትጥቅ አስፈቺ ዜማዎችን ብቻ እንዲዜሙ ወያኔ እቀባ ማድረጉ፤ ወኔ የሚሰነፍጡ የጀግንነት ዜማዎች ቢዜሙ፤ በሚፈጥሩት ሕዝባዊ ትኩሳት እንዳይለበለብ በመፍራት፤ ለቅሶ መሰል፤ የተስፋ መቁረጥ፤ እድልን የሚያማርሩ፤ ወንድ አስለቃሽ ዜማዎች ብቻ በማሰራጨት፤ የወጣቱን ልብ ያቀልጣል ወኔውንም ያኮላሻል ። ኢትዮጵያዊ ልምድና ብሂላችን የሚለን፤*
**« ወንድ ልጅ በልቡ እንጂ በዐይኑ ኢያለቅስም » ነውና ጎበዝ ሰንፈጥ እንበል !!**

*ሌላው እጅ ለእጅ ተያይዘን አንድ መሆናችንን በማሳየት ወያኔን ማሳፈር ሲገባን፤ ጎንደሬው ጎንደርን ብቻ ሲከረክምና ሲነቅስ፤ ጎጃሜው ጎጃምን ብቻ ሲኩልና ሲነቃቅስ ሸዌው ሸዋን ብቻ ሲያሞግስ፤ ወለጋው አሾኮኮ ያ ጃሌ ሲል፤ ሐረሪው ወሪ እማይለሌ… ወዘተ እያልን፤ ወያኔ እንደፈለገው ፡ እያንዳንዱ ጎሳ ፈሳም ዝንጀሮ ይመስል፡ ተራርቆ ለየብቻው እንዲያላዝን እንጂ ፡ ተቀራርበው እንዲወያዩ፤ እንዲነጋገሩና እንዲተባበሩ ስለማይፈልግ፤ እሱ ቆፍሮ ባዘጋጀው የዘረኝነት የቆሻሻ መውረጃ ቦይ ውስጥ ኮለል ብለን ስንወርድለት ልቡ በደስታ ጮቤ ይረግጣል ።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !*
*ሐምሌ 27/ 2002 ዓ.ም. (Augest 3/2010)*

EthioLion

EthioLion.com